# አንቺ አኬልዳማ መተማ !

በዪ እስቲ ተናገሪ አፍ አውጪ መተማ
የት ነው የደበቅሽው የፅዮንን ግርማ ?
ሓቅን ቀብረሽ ተሰማራሽ አሉ ውሸትን ለቀማ
ለእውነት ያልታደልሽው አንቺ **አኬልዳማ፤**

አንገቱን በሰይፍ ቀልተሽ የጣልሽው
ለውሾች መጫወቻ ስጦታ ያበረከትሽው
ስጋውን በልተሽ ደሙን የጠጣሽው
አጥንቱ አመድ አድርገሽ የፈጨሽው
ይባስ ብለሽ እፍኝ አፈር ነፈግሽው
በዪ እስቲ ተናገሪ አፍ አውጪ መተማ
የት ነው የደበቅሽው የፅዮንን ግርማ ?
ሓቅን ቀብረሽ ተሰማራሽ አሉ ውሸትን ለቀማ
ለእውነት ያልታደልሽው አንቺ **አኬልዳማ፤**

ያ የጉንደት የጉራዕ ፊተውራሪ
ያ የሰሓጢ የዶግዓሊ ፊተውራሪ
ያ የፅዮን ጌታ የቀይ ባሕር አንበሳ
ያ የሓበሻ መከታ የህንድ ውቅያኖስ አንበሳ
ያ የሴም፣የካም፣የናይሎቲክ ጋሻ
ያ ቅን አሳቢ የዋህ የሌለው አበሳ
ያ አንገቱን የሰጠሽ ህይወቱን ሳይሳሳ
ቸል ብለሽ ደሙን አሳልፈሽ ለወጠምሻ
ርስቱን አደረግሽው አሉ የቀበሮዎች ዋሻ

በዪ እስቲ ተናገሪ አፍ አውጪ መተማ

የት ነው የደበቅሽው የፅዮንን ግርማ ?

ሓቅን ቀብረሽ ተሰማራሽ አሉ ውሸትን ለቀማ

ለእውነት ያልታደልሽው አንቺ አኬልዳማ፤

አንቺ አስመሳይ ወለዋይ ነገር

ጉያሽ ውስጥ የተሰራው ዘለዓለማዊ ተአምር

ሓቁን ጥላሸት ቀብተሽ እንክርዳድ ዘርተሽ

ውዥንብር

አካሉን ቆራርጠሽ መነዘርሽው በገሃድ በስውር

ድካሙን ከንቱ አስቀርተሽ ሰው በሌለበት አገር

በሁለት ቢለዋ አርደሽ ከተትሽው መቃብር

ከከሓድያን አብረሽ ተዘባበትሽው የቀራንዮን ፍቅር

ግዜውን ጠብቆ እውነት መውጣቱ ላይቀር

ትዝብት አስቀረሽ እንጂ እውነት አይቀበር

አንቺ ውለታ ቢስ አኬልዳማ ምድር

በዪ እስቲ ተናገሪ አፍ አውጪ መተማ

የት ነው የደበቅሽው የፅዮንን ግርማ ?

ሓቅን ቀብረሽ ተሰማራሽ አሉ ውሸትን ለቀማ

ለእውነት ያልታደልሽው አንቺ አኬልዳማ፤

እውነትን መስክሪ አንቺ አኬልዳማ መተማ

!

መጋቢት 1/2007 ዓ.ም

መታሰቢያነቱ :"ለስዩመ እግዚአብሔር ዮሃንስ ራብዓዊ"

ንጉሰ ፅዮን ንጉሰ ነገስት ዘኢትዮጵያ

ብይፍጠር ኪ/ማርያም

03-09-16